# የዜጎች የአቤቱታ ደብዳቤዎች ከጋሞጎፋ

## ማስታወሻ

*ከዚህ በታች የሚያነቧቸው የአቤቱታ ደብዳቤዎች በኮምፒዩተር ከመገልበጣቸው በቀር የተጻፉት በሰለባዎቹ በራሳቸው ነው፡፡ አማርኛ የመጀመሪያ ቋንቋቸው አይደለም፡፡ በደብዳቤዎቹ ውስጥ የሚያገኟቸውን የቃላት ግድፈቶችም በዚህ መንፈስ በመረዳት አስተካክለው ያንብቡት፡፡ በደብዳቤዎቹ ውስጥ አንዳንድ ቃላትን ግልጽ ለማድረግ ብቻ ሲባል በቅንፍ ውስጥ ማስተካከያ ተመልክቷል፡፡*

## አቤቱታ አንድ

**ቀን፡ 23/9/2002**

ስም ከነአያት፡ *(ለደህንነታቸው ሲባል የሁሉም ተበዳዮች ማንነት እዚህ አልተገለጸም)*
እድሜ፡ ------------
ጾታ፡ -----------
የመኖርያ አካባቢ፡ *ጋሞጎፋ ዞን፤ ዳራማሎ ወረዳ፤ ሚስታ ቀበሌ*
በደል የተፈጸመበት ቀን፡ **15/9/2002**
የበደሉ መንስኤ፡ ምርጫ **(2002)**

### ዝርዝር ሃሳብ

በምርጫ ሳምንት በቀረበበት ወቅት ወዴ እኔ ቤት ውስጥ ተቀምጬ እያለው ቤቴ መጥተው በምርጫው ጉድ ይሆናል፤ ተቃዋሚን የመረጠ ሰው ሁሉ ይደበደባል፤ ምርጫው ካለፈ ከአገር እናባርራለን፡፡ በጨለማ ዱራ (ዱርዬ) ገዝተን እቤታቼውን በድንጋይ እናስመታለን ስሉ ፈርቼ እያለሁኝ የምርጫው ቀን ከሰፈር አንስቶ እስኬ ምርጫ ጣቢያ ድረስ እናንቴ ንብን ብቻ ምረጥ ንብን ካልመረጥክ በሽምግልና ትገረፋላችሁ እያለ ካሉ በኋላ ሄደን እኔ ተለይቼ ወደ ሰልፌ ውስጥ ገብተናል፡፡ እቤት (መምረጫው ክፍል) ስገባ ብቻዬን ሳይሆን የቀበሌው አስተዳደር ፊርምያውን (ፊርማውን) በምፈርም ሰዓት መስኮት በተፈጠረ ቦታ ቆም ብሎ እያዩ እኔ ምርጫውን መረጥኩት፡፡ በቀን 21/9/2002 ማታ ቤቴ በድንጋይ በመምታት አሁንም እኔን ያባርራሉ እያለሁት ነው፤ እየሰጋሁ ነው፡፡ አሁንም ዛሬ ቀንም ፖሊስ መቱዋል እስከ መስከረም (2003) ድረስ በድብደባ ያባርራሉ በማለት ይገኛል፡፡

ስለሆነም ይህን ምርጫ ምክንያት ለእኔ ስጋት በመሆን ስገባ ስወጣ እየሰጋሁት ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን ማስፈራራት እንድቆም እጠይቃለሁኝ፡፡ ያለበለዚያም በምርጫ ቢቀር የተሻለ ነው በማለት አስተያየቴን እያስቀመጥኩት ስጋቴ ይቁም እላለሁኝ፡፡

የግራ ሌባ ጣት ፊርማ
የተበዳይ ሙሉ ስም

---

## አቤቱታ ሁለት

**ቀን፡ 24/9/2002**

ስም ከነአያት፡ ------------------------------------------
እድሜ፡ ------------
ጾታ፡ ------------
የመኖርያ አካባቢ፡ *(ጋሞጎፋ ዞን)፤ ዳራማሎ ወረዳ፤ ሚስታ ቀበሌ*
በደል የተፈጸመበት ቀን፡
በደሉን የፈጸመ አካል፡ *የቀበሌ አስተዳደር አቶ ክብርአለም በልሁ*

### ዝርዝር ሃሳብ

በምርጫ ቀን እኔ ለምርጫ ስሄድ እኔ ለመምረጥ ምርጫ ጣቢያ ፖልስ ያልታወቀ ይመጣል፤ ምርጫውን ካልመረጣችሁ ትባረራላችሁ ከዚህ መንግሥት ሌላ ማንም የለም በማለት አስጠንቅቆ በተፈጠረው መስኮት እኔ ስመርጥ ይመለከተኝ ነበር፡፡ እኔ ፈርቼ ንብን ያለውዴታዬ መርጫለሁ፡፡ ከምርጫ በኋላ ፖሊስ ይመጣል በእኛ ብሎክ (የመኖርያ ሰፈር ውስጥ) አምስት ሰው አልመረጠም፤ እነዝያ ይባረራሉ በማለት በስጋት ላይ ነኝ፡፡ በምርጫ ሰሞን መንግሥት የለም ከሞታችሁ ደም ከልብ ናችሁ ተጠንቀቁ እያሉ ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ እጁ ላይ ቀለም የሌለው ሁሉ ይደበደባል፤ ይጠፋል ብሉዋል፡፡ ስለዚህ ይህ ስጋት ስላለኝ ማስፈራሪያ ይቁም እላለሁኝ፡፡

የቀኝ ሌባ ጣት ወይም ጠቋም ጣት (አሻራ ፊረማ)
የተበዳይ ሙሉ ስም

ቀን: 24/9/2002

<u>አቤቱታ ሦስት እና አራት</u>: (ሁለት ተበዳዮች ናቸው)

ስም ከነአያት: ------------------------------------------------- እና -------------------------------------------------
እድሜ: ------------ ----------------- ጾታ: --------- ------------
የበደሉ መንስኤ: <u>የምርጫ</u> (2002)
በደሉን የፈጸመ አካል: <u>የቀበሌው አመራር እና የሰ(ሴ)ል አመራር</u>
በደሉ የተፈጸመበት ቀን: <u>15/9/2002</u>
የመኖርያ አድራሻ: <u>ድታ ወረዳ ቱካና ጋና</u>

## <u>የበደሉ ዝርዝር</u>

በምርጫ ወቅት እኛ ያለውዴታ ተገደን የቀበሌ አመራር በሙሉ ከመንደር እስከ ምርጫ ክልል ድረስ ወንበር ይዘው ተቀምጠው የድርጅት አመራርና የሰል (ሴል) አመራር ሁሉ ንብን ካልበረጣችሁ ትታሰራላችሁ ለእናንተ ሥራ አይሰጥም ጦር ይመጣል፤ በ97 ምርጫ ላይ ብዙ ሰው ሞቷል፤ ችግር ተፈጥሩዋል፤ ብለዋል:: ካልመረጣችሁ ሰፍትነት የምትጠቀሙ አትጠቀሙም በማለት አስፈራርተዋል:: አንድ ሰው የቤተሰብን ሁሉና የጎረቤትን የምርጫ ካርድ ሰብስቦ ይመርጣል:: አስመራጭ ሰው በምሥጥር (ድምጽ) መስጫ ውስጥ ቁጭ ብሎ እጅን ይዞ ብቻውን ጣትን በመያዝ በንብ ላይ ያስመርጣል:: ምስጥራዊ አይደለም:: አንድ ሰው ታሞ ከቀረ የምርጫ አስፈጻም ብቻውን ይመርጣል::

ስለሆነም ይህ ፍትሕ ያልሆነ ምርጫ ስለሆነ እኛ ---------------------- ሆነን ህደቱ ስናይ ቅር አሰኝቶናል:: ያልፈለግነውን ለመምረጥ ተገደናል::

የግራ ጠቋም ጣት (አሻራ ፊርማ)
ሙሉ ስም

የቀኝ ጠቋም ጣት (አሻራ ፊርማ)
ሙሉ ስም

---

<u>አቤቱታ አምስት</u>

ቀን: 24/9/2002

ስም --------------------------------------------------- ዕድሜ: ------------

እኔ ------------------------------------------------------------------------------------------ ያጋጠመኝ ችግር ብዙ ብሆንም አብዛኛውን ግዜ የውሸት መረጃ ተመስክሮብኝም እስክቅጣ ግዜ ታግያለሁ:: ከምርጫ 97 እስከ አሁን:: ነገር ግን የአሁኑ ምርጫ ትዝታ አስቀምጦብኛል::

በድታ ወረዳ ውሎ ቆጼ ተራራ ወጥቴ(ቼ) እኔ መረጃውን ስወስድ የኢህአዴግ ካድሬ መጣና አንቴ ምን ትጽፋለህ ብሎኝ ሰዎችን ከመበተኑም በላይ አንቴ ምን ትጽፋለህ ብሎኝ እንደምንም ብዬ እኔ ደብዳቤ ጽፋለሁኝ ብልም ናና አሳየኝ የፃፍከውን አምጣ ብሎኝ ስቀማ አፈትልኬ በእሩጫ አመለጥኩትና የድታን (የወረዳ ስም ነው) ሳገኝ ቻልኩት::
ስለዝህ የመፃፍና የማንበብ መብት ለሠው ልጅ መቸ ይሰጣል በሐገራችን እላለሁኝ::

ሙሉ ስም
የጽሁፍ ፊርማ